# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOL
# የምግብና ስነምግብ አገልግሎቶች ክፍል

MY SCHOOL BUCKS

MySchoolBucks ወላጆች በኢንተርኔት የልጃቸውን የካፍተሪያ አካውንት የቅርብ ጊዜ ግዥዎችን ለመመልከትና የቁርስ፣ የምሳና (a la carte) ላ ካርቴ ምግቦች የቅድሚያ ክፍያ እንዲፈጽሙ የሚያስችል አማራጭ አገልግሎት ነው። ይህ አገልግሎት የቀረበው ፍላጎት ላላቸው ቤተሰቦች ምቾት ነው። ደህንነቱ የተጠበቀ የኦን ላይን አካውንት በመክፈት ወላጆች የልጃቸውን አካውንት መቆጣጠር/መከታተል ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| ቀላል | ምዝገባና ገንዘብ መክፈል ቀላል ሲሆን በኦን ላይን ላይ ያልቃል። |
| ተስማሚ/የሚመች | አካውንትዎ አንድ ጊዜ ከተከፈተ በኋላ፣ ባላንሶችን ማየት ይችላሉ፣ የተማሪ ግዥዎችን ይመልከቱና በከምፒዩተርዎ ለልጅዎ አካውንት ገንዘብ ያስገቡ። |
| ደህንነቱ የተጠበቀ/አስተማማኝ | የግልዎና የክፍያ ካርድዎ መረጃ በከፍተኛ ደረጃ የኢንተርኔት ደህንነት የተጠበቀ ነው። |
| አንድ ጊዜ | በዚህ የአቶማቲክ ክፍያ አማራጭ፣ ገንዘብ ሁል ጊዜ በልጅዎ አካውንት ይገኛል። ዝቅተኛ ባላንስ ውስጥ ሲደርስ፣ ገንዘብ በአቶማቲክ ይገባል/ይጠራቀማል። |
| የዝቅተኛ ባላንስ የኢ-ሜይል ማሳሰቢያ | ወላጆች የልጃቸው አካውንት ባላንስ ዝቅ ባለ ጊዜ የኢ-ሜይል መልእክቶች ማግኘት ይችላሉ። |
| በቀጣይ ቀን የመገኘት ሁኔታ | የቅድሚያ ክፍያዎች በአጠቃለይ በሚቀጥለው ቀን በት/ቤቱ ይገኛል። |

## የምዝገባ 4 ቀላል ደረጃዎች/እርምጃዎች

| 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|
| www.MySchoolBucks.com የሂዱና"Sign up today!"ን ይጫኑ | ለራስዎት አካውንት ይክፈቱና፣ ልጅዎን ይጨምሩት/ይጨምሯት። የተማሪው/ዋ ስም ያስፈልግዎታል (ልክ በሪፖርት ካርድ ላይ እንደሚጻፈው)፣ ት/ቤት፣ ክፍል፣ የትውልድ ቀንና፣ ባለ 6 ዲጅት የተማሪ መታወቂያ ቁጥር (ፒን አይደለም)። | (እንደ አማራጭ) ለልጅዎ የካፍተሪያ አካውንት የቅድሚያ ክፍያ ማድረግ ከፈለጉ፣ የዴቢት ወይም ክረዲት ካርድ መረጃ ያቅርቡ። | ለልጅዎ የቅድሚያ ክፍያ ለማድረግ የምግብ ክፍያ አማራጭ ይምረጡ ወይም፣ የቅርብ ግዜ የካፍትሪያ ግዥዎችን ለማየት የልጅዎን ስም ይምረጡ። |

### ጠቃሚ

ለእያንዳንዱ የክፍያ ልውውጥ/ግብይት የ$1.95 "የአማራጭ ክፍያ"/convenience fee/ አለ። ሁሉም ክፍያዎች በክፍያ ጊዜ ይታያሉ። አካውንት ለመፍጠርና የልጅዎን አወጣጥ ታሪክ ለማየት ወይም አካውንቱ ዝቅተኛ ሲሆን የሚሰጠውን ማሳሰቢያ ለማግኘት ምንም ወጭ የለም። ይህንን አገልግሎት በማቅረብ ት/ቤቱም ሆነ የምግብና የስነምግብ አገልግሎቶች ክፍል የሚያገኙት ምንም አይነት ገቢ የለም። ክፍያዎች ከኦን ላይን ክሬድት/ዴብት ካርድ ክፍያዎች ከማስፈጸም ጋር የተያያዙ ናቸው። ይህ አገልግሎት እንደ አማራጭ የቀረበ ነው - ት/ቤቶች ለካፍተሪያ ምግቦች ቼኮችንና ጥሬ ገንዘቦችን መቀበል ይቀጥላሉ።

በምዝገባ ጊዜ እርዳታ ቢፈልጉ ወይም ስለአካውንትዎ ስለሚኖርዎት ጥያቄዎች የMySchoolBucksን የደንበኛ እርዳታ የነጻ/toll-free/ ስልክ በዚህ 1-855-832-5226 ይደውሉ።